International Child Development Initiatives

ESD



# ደስተኛ ህጻናት ተማሪዎች

## የለጋ ህጻናት ስነልቦናዊና ማህበራዊ ደህንነት በኢትዮጵያ

## ጥቅል ሪፖርት

## መግቢያ

ይህ ሪፖርት በአማራና በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል እድሜያቸው 5 ዓመት የሆናቸው ህጻናት የስነልቦናዊና ማህበራዊ ደህንነት ዙሪያ ከ2008-2010 ዓ.ም በተካሄደ ጥናትና ፕሮጀክት ትግበራ ዋና ዋና የጥናቱ ውጤቶች፣ ቅድመ መደበኛ ትምህርትን ለማሻሻል በፕሮጀክቱ የተከናወኑ ተግባራቶችና ደስተኛው ህፃን ተማሪ በኢትዮጵያ የተሰኘውን አጭር ዘጋቢ ፊልም የያዘ ሲሆን ይኸውም የቅድመ መደበኛ ትምህርት አተገባበርን፣ የቅድመ መደበኛ መምህራን ትምህርት ስልጠናና ፖሊሲ ለማስተዋወቅ ይረዳል፡፡

ፕሮጀክቱ ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኘው ኢ.ኤስ.ዲና ኒዘርላንድ ውስጥ በሚገኘው አይ.ሲ.ዲ.አይ በተባሉ ድርጅቶች በጋራ ትብብር የተከናወነ ነው፡፡

ማጣቀሻ ምንጮች:

Both, R., Cortellesi, G., Gebre, K., Kernan, M., Mussie, A., Sehalu, A. (2018) *Happy young learners: psychosocial well-being of young children in Ethiopia. Summary report.* Addis Ababa: ESD and Leiden: ICDI.

©ICDI and ESD, June 2018

ፕሮጀክቱና የምርምር ስራው በድዮራፍት ፋዉንዴሽን በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ የተከናወነ ነው

## ስነልቦናዊና ማህበራዊ ደህንነት ማለት ምን ማለት ነው?

የስነልቦናዊና ማህበራዊ ደህንነት ማለት ህጻናት ከአዋቂዎችና ከዕድሜ እኩዮቻቸው ጋር ቅርብና ጥብቅ የሆነ ግንኙነት መፍጠር መቻል፤ ልምዳቸውን፣ ስሜታቸውን ከአካባቢው ማህበረሰብና ባህሉ መሰረት መግለፅ መቻል፤ አካባቢያቸውን ማወቅ እንዲሁም መማር መቻል ማለት ነው (ሴንተር ኦን ሶሻል ኢሞሽናል ፋዉንዴሽንስ ፎር አርሊ ለርኒግ፡ 2008)፡፡

ለህጻናት ስነልቦናዊና ማህበራዊ ደህንነት ትኩረት መስጠት በቅድመ መደበኛ ት/ት ጥራት ላይ የጎላ ሚና ይጫወታል፡፡ በተጨማሪም በህጻናት የወደፊት ህይወት ላይ ስሜታዊ፣ ማህበራዊ፣ ትምህርታዊና ኢኮኖሚያዊ የሆኑ አወንታዊ ውጤቶች እንዲኖሩ ያደርጋል፡፡

የህጻናት ስነልቦናዊና ማህበራዊ ደህንነት ጉዳይ ትኩረት ማነስ የህጻናት የማደግና የመማር አቅማቸውን ያቀጭጨዋል፡፡

## ጥናቱ ያካተተው ነገር ምንድን ነው?

የዚህ ጥናት ዋና አላማ/ትኩረት በአማራ ክልል በሰሜን ሸዋ ዞንና በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ሲዳማ ዞን የሚገኙ 1000 ህጻናት (526 ሴቶችና 474 ወንዶች) በከተማ፣ በከፊል ገጠራማና በገጠር የቅድመ መደበኛ ት/ቤቶች ገብተው የሚከታተሉ ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት ከእያንዳንዱ ህጻናት ስነልቦናዊና ማህበራዊ ደህንነታቸው ዙሪያ በመምህራኖቻቸው በመታገዝ አይ.ሲ.ዲ.አይ ባዘጋጀው መጠይቅ መሰረት መረጃ አሰባስበናል፡፡ የመጠይቁ ይዘትም ህጻናት በቤታቸውና በት/ቤታቸው ያላቸው አጠቃላይ ሁኔታና ባህሪ ምን እንደሚመስል የሚያሳይ ነው፡፡ በተጨማሪም ከርዕሰ መምህራኖች፣ ከወላጆች፣ ከመምህራን አሰልጣኞችና ከት/ት ጽ/ቤት ባለሙያዎች ጋር የቡድን ውይይት ተካሄዷል፡፡



# ዋናዋና የጥናቱ ውጤቶች/ግኝቶች

- ህጻናት ልጆች በቤት ውስጥ የሚገጥሟቸው ችግሮች ለምሳሌ ድህነት፣ በአንድ ወላጅ ማደግ (ከእናታቸው ወይም ከአባታቸው ብቻ)፣ ወላጅ አልባ መሆንና የመጽሀፍትና የመጫወቻ አለመኖር ከብዙዎቹ ጥቂቶቹ ናቸው፡

- በሰሜን ሸዋ ዞን በከተማ አካባቢ የሚኖሩ ወላጆች ለህጻናት ልጆቻቸው በቂና ምቹ የሆነ የመጫወቻ ስፍራ ባቅራቢያቸው አለመኖሩን ገልጸዋል፡፡

- በአንጻራዊነት በገጠር አካባቢ የሚኖሩ ልጆች በነጻነት የፈለጉትን አይነት ጨዋታ ከእድሜ እኩዮቻቸውና ከወንድም ከእህቶቻቸው ጋር ይጫወታሉ፤ በሌላ በኩል እነኚህ ህጻናት አብዛኛውን ጊዜ በለጋ እድሜያቸው ብዙ ሀላፊነቶችን ይሸከማሉ፡፡

- ይህ ጥናት በሁለቱም ክልሎች ህጻናት በቅድመ መደበኛ ት/ቤት ገብተው ክፍል ውስጥ የመገኘት ምጣኔያቸው ደካማ እንደሆነ ያሳያል፡፡ በአንድ በኩል ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ት/ቤት ለመላክ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ማሟላት ስለማይችሉ ጭንቀት ውስጥ ይገባሉ በሌላ በኩል በአብዛኛው ወላጆች ለልጆቻቸው በቂ የሆነ ልብስ፣ ምግብና የት/ት ቁሳቁሶች ለማሟላት አቅም የላቸውም፡፡

- በአማካይ የቅድመ መደበኛ ተማሪዎች የክፍል ምጣኔ 51 ሲሆን በአንጻራዊነት በገጠር አካባቢ የሚገኙ ት/ቤቶች ከፍተኛ የሆነ የክፍል ምጣኔ አላቸው፡፡

- በህጻናት የአእምሮ እድገት ላይ ያላቸው የእውቀት ውስንነት፣ ለጋ ህጻናትን የማስተማር ክህሎት ማነስ፣ የማስተማሪያ ግብዐቶችና ቁሳቁሶች እጥረትና የመማሪያ ክፍሎቹ ምቹ አለመሆን በቅድመ መደበኛ መምህራን ላይ ያሉ ዋነኛ ችግሮች/ስጋቶች ናቸው፡፡

- በጥናቱ ላይ ከተሳተፉት 1000 ህጻናት መካከል 37 ፐርሰንት የሚሆኑት የስነልቦናዊና ማህበራዊ ደህንነት ችግሮች ያሉባቸው ሲሆን ይህም በገጠርና በከፊል ገጠራማ ከሚኖሩት ህፃናት ጋር ሲነፃፀር ችግሩ በከተማ አካባቢ ጎልቶ ይታያል፡፡



# የመፍትሄ ሀሳቦች

## የህጻናት የስነልቦናዊና ማህበራዊ ደህንነት- ከንድፈ ሀሳብ ወደ ትግበራ

የመፍትሄ ሀሳቦች ለመምህራንና ለመምህራን አሰልጣኞች)



የቅድመ መደበኛ ት/ት አገልግሎት አሰጣጡን ለማጎልበት የመምህራን ኮሌጆች (በቅድመ አገልግሎት ስልጠና የሚሰጡ የት/ት አይነቶች) እና ሌሎች ስልጠናውን የሚሰጡ አካሎች (ስራ ላይ እያሉ የሚሰጥ ተጨማሪ ስልጠና) በህጻናት ስነልቦናዊና ማህበራዊ ደህንነት ዙሪያ ትኩረት ሰጥተው ሊሰሩ ይገባል። በዚህም መሰረት በስልጠናው የህጻናት ስነልቦናዊና ማህበራዊ ደህንነት ማለት ምንድነው፣ ለምንስ አስፈለገ፣ ለህጻናት ምቹ የሆነ የመማር ማስተማር ሁኔታ (በክፍልና ከክፍል ውጪ) እንዴት መፍጠር ይቻላል የሚሉት ጉዳዮች መካተት አለባቸው።

## ስነልቦናዊና ማህበራዊ ደህንነትን እንደ ፖሊሲ አጀንዳ መውሰድ

የመፍትሄ ሀሳቦች ለአካባቢና ለብሄራዊ ፖሊሲ አውጪዎች

የዚህ ፕሮጀክት የጥናት ውጤት ለውጡን ለማየትና ለመለካት በየሁለት አመት ልዩነት ጥናት በማካሄድ፤ የህጻናት ስነልቦናዊና ማህበራዊ ደህንነት የት/ት ፖሊሲ አውጪዎች ቅድሚያ ሊሰጡት የሚገባ ጉዳይ መሆን አለበት። በተጨማሪም በሌሎች የኢትዮጵያ ክልሎች ላይ በህጻናት ስነልቦናዊና ማህበራዊ ደህንነት ዙሪያ ጥናቶች ሊደረጉ ይገባል።

በቅድመ መደበኛ ት/ት ላይ በየጊዜው/በተከታታይ ጥናቶችን ማካሄድ በህጻናት ስነልቦናዊና ማህበራዊ ደህንነት ጉዳይ ትኩረት እንዲጨምር ያደርጋል፤ አዳዲስ ፖሊሲዎች እንዲወጡ ያደርጋል፤ ፈጠራን ያበረታታል፤ ሌሎች አዳዲስ ጥናቶች እንዲካሄዱ ያነሳሳል፤ ስልጠናዎች እንዲሰጡ ያደርጋል፤ የሀገሪቱን ህጻናት ልጆች ለመርዳት ያገለግላል።




## የህጻናት የስነልቦናዊና ማህበራዊ ደህንነት ለመደገፍ ቤተሰብ፣ ማህበረሰቡና ት/ቤቶች በጋራ መስራት አለባቸው

የመፍትሄ ሀሳቦች ለመምህራንና ለመምህራን አሰልጣኞች



መምህራን ከወላጆችና ከማህበረሰቡ ጋር በመከባበር፣ መልካም ግንኙነት በመፍጠርና የተለያዩ ስልጠናዎችን በመስጠት በጋራ መስራት አለባቸው፤ በዚህ መሰረት ህጻናት ከአዋቂዎችና ከእድሜ እኩዮቻቸው ጋር መልካም ግንኙነት እንዲኖራቸው ያደርጋል፤ በቤትና በት/ቤታቸው ውስጥ ያከናወኑት የየዕለት ተግባራትን ለወላጆቻቸውና ለማህበረሰቡ መናገር ይችላሉ።

## የህጻናትን ደህንነት በኢትዮጵያ ለማስተዋወቅ የሚረዳ ስልት

የመፍትሄ ሀሳቦች ለአካባቢና ለብሄራዊ ፖሊሲ አውጪዎች

የአንድ ጊዜ ጥናት ለህጻናት ልጆች አካላዊ፣ ማህበራዊና አካባቢያዊ እድገት በየደረጃው ለማህበረሰቡ፣ ለዞኑና ለክልሉ ትልቅ ጠቀሜታ ይሰጣል።

እያንዳንዱ ባለድርሻ አካላት (ጤና፣ ት/ት፣ የገጠርና የከተማ ልማት ጽ/ቤቶች) በህጻናት እድገት ደህንነት ዙሪያ ስትራቴጂ አውጥተው በጋራ መስራት አለባቸው። ይህም ማለት ህጻናት በየጊዜው የጤናቸውን ሁኔታ መከታተል፣ በአቅራቢያቸው ምቹ የሆነ የመጫወቻ ስፍራ ማመቻቸት፣ ወደ ት/ቤት በሚሄዱበት ወቅት ምቹ መንገድ መፍጠርና የቅድመ መደበኛ ት/ቤቱን ማበረታታት ናቸው።



# የጥራት ማሻሻያ ፕሮግራም

የፕሮጀክቱን የጥናት ውጤት መሰረት በማድረግ፣ በሰሜን ሸዋና ሲዳማ ዞን በሚገኙ በ4 ቅድመ መደበኛ ት/ቤቶች ላይ የሚገኙ ወላጆችና መምህራን በጋራ በመሆን የህፃናትን የስነልቦናዊና ማህበራዊ ደህንነት ለማሻሻል የድርጊት መርሀ ግብሮች/ እቅድ አዘጋጅተዋል። በዚህም መሰረት 300 የሚሆኑ ለጋ ህጻናት (በሁለቱም ጾታ) ተጠቃሚ ሆነዋል።



በወላጆችና በመምህራን የተለዩ ተግባራቶች የሚከተሉት ናቸው

- ወላጆችን በማሳተፍ የትምህርት ቤቶችን ሁኔታ ማሻሻል
- ት/ቤቱን ሳቢና ደህንነቱ የተጠበቀ ማድረግ
- ለቅድመ መደበኛ መምህራን ስልጠና መስጠት








የተገኙ ውጤቶች

## ት/ቤቶችና መምህራኖች

- የቅድመ መደበኛ መምህራን ባገኙት ስልጠና መሰረት የማስተማር ክህሎታቸው አድጓል፤ ከህጻናት ጋር ያላቸው ግንኙነት ጨምሯል። በተጨማሪም መምህራን ለህጻናት ልጆች አዳዲስ የመማሪያ ቁሳቁሶችን በማሳየት በመማር ማስተማሩ ሂደት የበለጠ ደስተኛ እንዲሆኑ አድርጓል።
- የቅድመ መደበኛ መማሪያ ክፍሎች በአካባቢው በሚገኙ ቁሳቁሶች ታድሰዋል፤ አሁን በክፍሎች ውስጥ በቂ የሆነ ወንበርና ጠረጴዛዎች፣ የመማሪያ ቁሳቁሶችና መጫዎቻዎች ይገኛሉ።
- የቅድመ መደበኛ የመማሪያ ክፍሎች ግንባታ ለህጻናት ምቹና ደህንነቱ የተጠበቀ ሆኗል፣ የት/ቤቱም ግቢ በአጥር ተከልሏል።

## ህጻናትና ወላጆች/ቤተሰቦች

- በት/ቤት ውስጥ የወላጆች ተሳትፎ ጨምሯል፤ ወላጆችም የቅድመ መደበኛ ት/ቤቶችን ለመርዳት ከፍተኛ ፍላጎት አሳይተዋል።
- ህጻናቶች በነፃነት ሰፊ የሆነ የመማሪያና የመጫወቻ ጊዜ እንዲኖራቸው ሁኔታዎች ተመቻችቶላቸዋል፡ ፡ በዚህም ምክንያት ህጻናቱ በጣም ደስተኛ ሆነዋል፣ ከእድሜ እኩዮቻቸውና ጋር መጫወት ችለዋል፣ የንግግር ክህሎታቸው ጨምሯል፣ ፍርሀታቸው ቀንሷል፣ በራስ የመተማመን ብቃታቸው ጨምሯል።

# የተማሪዎችና የመምህራን ድምፅ/ መምህራንና ተማሪዎች ከተናገሩት

## 1. ምስራቅ በር አንደኛ ደረጃ ት/ቤት፣ ሀዋሳ ከተማ




መምህራን ከሰጡት አባባል/ጥቅስ፦ እኔ በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጪ መጫዎቻዎች መኖራቸው በህጻናት አጠቃላይ እድገትና ደህንነት ላይ ያላቸውን ሚና በደንብ ተመልክቻለሁ፤ ይኸውም ከጓደኞቻቸው ጋር ለመጫወትና መልካም ግንኙነት እንዲኖራቸው ዕድል ፈጥሯል። ለኛ ለመምህራን ራሱ የት/ት ጊዜው አስደሳችና አመርቂ እንዲሆን አድርጓል። ስለዚህ በህጻናት ላይ መስራት ለማህበረሰቡ የሚሰጠው ጥቅም የጎላ ነው።

**ታደለች አየለ- መምህር**

ህጻናት ከሰጡት አባባል/ጥቅስ፦ ከጓደኞቼ ጋር መጫወት እወዳለሁ በተለይ ደግሞ እሽክርክሪትና ሸርተቴ መጫወት ያስደስተኛል።

**ዮሴፍ መለሰ- የ6 ዓመት ተማሪ**




## 3. አንድነት ቅድመ መደበኛ ት/ቤት፣ ደብረ ብርሀን ከተማ

መምህራን ከሰጡት አባባል/ጥቅስ፦ እኔ በጣም ተደንቂያለሁ/ተገርሜያለሁ፤ በአጭር ጊዜ ውስጥ በተወሰነ ግብዐቶችና ቁሳቁሶች ብዙ አመርቂ የሆኑ ስራዎችን አከናውነናል። በተጨማሪም መምህራንና ወላጆች በጋራ መስራታቸው ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለው ተምሬያለሁ። አካባቢው ላይ በሚገኙ ግብዐቶችና ቁሳቁሶች በመጠቀም ህይወትን ቀለል ማድረግ ይቻላል።

**የሺ ታጠቅ- መምህር**

ህጻናት ከሰጡት አባባል/ጥቅስ፦ እኔ በመምህሮቼና በት/ቤቴ ደስተኛ ነኝ፤ ት/ቤታችን ውስጥ ብዙ መጫዎቻዎች አሉ፤ መምህራኖቻችንም እንደ እናት ይንከባከቡናል ከነሱ ጋር መቆየት እፈልጋለሁ።

**በቀለ ደስታ- የ5 ዓመት ተማሪ**




## 2. ኩርዳ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት፣ ቱላ ክ/ከተማ



መምህራን ከሰጡት አባባል/ጥቅስ፦ እዚህ ት/ቤት ትንሽ ቆይቻለሁ ከዚህ ቀደም በት/ቤቱ ያላየሁትን ነገር አይቻለሁ፤ ህጻናቱ የጨዋታ ጊዜ አልነበራቸውም፤ አሁን ግን ብዙ የጨዋታ ጊዜ በመመደቡ የቅድመ መደበኛ ት/ት ጥራት እንዲጨምር አድርጓል። በህጻናቱም ላይ አወንታዊ የሆነ ለውጥ አይቻለሁ፤ ለወደፊት የህጻናት ህይወት ላይ ልዩነት ማምጣት ይቻላል።

**ጴጥሮስ ስምዖን- መምህር**

ህጻናት ከሰጡት አባባል/ጥቅስ፦ የመማሪያ ክፍላችን እንደዚህ አምሮ በማየቴ በጣም ደስ ብሎኛል፤ ት/ቤት ውስጥ ከጓደኞቼ ጋር ጎማ ላይ መጫወትን እወዳለሁ፤ በጣም ያስደስተኛል።

**ማሙሽ ሁሴን- የ6 ዓመት ተማሪ**

## 4. ድሬ ቅድመ መደበኛ ት/ቤት፣ ሲያደብርና ዋዩ ወረዳ

መምህራን ከሰጡት አባባል/ጥቅስ፦ የት/ቤቱ ብዙዎቹ ችግሮች ተፈተዋል፤ ህጻናቱም ት/ቤት በመቆየታቸው በጣም ደስተኛ ሆነዋል።

**አለምወሰን በፍቃዱ- መምህር**

ህጻናት ከሰጡት አባባል/ጥቅስ፦ ት/ቤት መቆየትን እመርጣለሁ፤ አንዳንዴ ወደ ቤት መመለስ እንኳን አልፈልግም።

**በረከት አብተው- የ6 ዓመት ተማሪ**



# ተጨማሪ ነገር ማወቅ ይፈልጋሉ?

ስለፕሮጀክቱ ተጨማሪ ነገሮች ማወቅ ከፈለጉ
በሚከተሉት ኢሜል አድራሻዎች ማግኘት ይችላሉ:


**ማርጋሬት ከርናን**
margaret@icdi.nl

**ወይም አእምሮ ሙሴ**
aemirom@esdethio.org


ሙሉ የጥናቱን ሪፖርት ማንበብና ደስተኛው ህፃን ተማሪ
ዘጋቢ ፊልም መመልከት ከፈለጉ የሚከተሉትን ድህረ
ገፆች ይጎብኙ:

www.esdethio.org

www.icdi.nl


ድጋፍ ያደረገው:
dioraphte